# የኢፌዴሪ የህጎች ግጭት አያያዝ ህግ ለማውጣት እንዲያግዝ የተዘጋጀ የመነሻ ጥናት

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ሰብለ ገ/ጊዮርጊስ

1. በውስጣቸው ባዕድ ነገር የያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚ የሚሆን የተደራጀ የሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግ በኢትዮጵያ ባለመኖሩ መሰል ጉዳዮችን ለመግዛት ዳኞች በተበጣጠሰ መልኩ የሚገኙ የተለያዩ ሕጎችን መሰረት በማድረግ የ ሚያጋጥሟቸውን ክርክሮች እንደሚፈቱ ከላይ በነ በሩት የ ዚህ ጥናት ክፍሎች ተመልክተናል፡ ፡ ከእነ ዚህ ሕጎ ች መሃከል በቀጥታ ተፈፃ ሚነ ት የ ሚኖራቸው የ ፌደራል ፍርድ ቤቶችን ሥልጣን ለመወሰን የ ወጣው አዋጁ ቁጥር 25/88፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግና የፍ/ብሔር ሕግ ናቸው፡ ፡ እነ ዚህ ሕጎ ች የ ሕጎ ች ግጭት አያያዝ ሕግ በባሕሪ የ ሚመለከታቸውን ጉዳዮች በተገ ቢው መልኩ ለመፍታት በቂ ባለመሆናቸው የ ተደራጀና ውስብስብ የ ሆኑነ ትን የ ሕጉን ጥያቄዎች በተገ ቢው መልኩ የ ሚደነ ግግ ሕግ ማፅደቅ አስፈላጊ ነው፡ ፡

2. በአሁኑ ወቅት የ ሕጎ ች ግጭት አያያዝ ሕግ ጉዳዮችን በተመለከተ በቀጥታ ተፈፃ ሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 25/88 ከጉዳዩ ውስብስብነትና አስቸጋሪነት አንፃር በቂ ያልሆነ እንዲሁም በርካታ ክፍተቶች ያሉት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል፡ ፡ ምክንያቱም አዋጁ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ የሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግ ደንቦችን ሳያካትትና መሰረታዊ መርሆችን ባላካተተ መልኩ በደፈናው የሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግ ጉዳዮች በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታዩ የሚደነግግ መሆኑ በቀዳሚነት የሚነሳ ጉዳይ ነው። በአጠቃላይ ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን ጥያቄዎችን በአግባቡ አለመመለስ እዚህ ጋር የሚታይ ችግር በመሆኑ የሚሰጡት ውሳኔዎች በውጭ አገር ባላቸው ተቀባይነትና አፈፃፀም ላይ ተፅእኖ ይኖራቸዋል። ሊዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው አዋጁ ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን ከሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግ የሚሰጠውን ትርጎሜ በአግባቡ ያላስቀመጠና የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ ነው። በተጨማሪም አዋጁ ዜግነ ትን ብቻ እንደአገናኝ ነገር መጠቀሙ ለሚፈጠሩትና ሊፈጠሩ ለሚችሉት ክፍተቶች እንደ ምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል። እንዲሁም የሕግ ምርጫን በተመለከተ የተቀመጡት ድንጋጌዎች በድጋሚ የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ያላስገቡ፣ የተከራካሪ ወገ ኖችን ጥቅም በአግባቡ የማያስከብሩ እንዲሁም የውጭ አገር ሕጎች በኢትዮጰያ ውስጥ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ መርሆችን

መሰረት በማድረግ ያልደነገጉ በመሆናቸው እንዲሁም ሕገ መንግስቱን የ መጣስ አዝማምያ በመሆናቸው ሊሻሩ ይገባል። ለዚህም የሚጠቀሰው በክልልና በፌደራል መንግስት ሕጎች መካከል ልዩኝቶች ቢፈጠሩ የትኛው የባለይነት ይኖረዋል የሚለውና በአዋጁ አንቀፅ 6(2) ላይ በተቀመጠው መሰረት የፌደራል ሕጎች የበላይነት ይኖራቸዋል፡ ፡ ይህ አሰራር በአብዛኞቹ ፌደራል አገራት ውስጥ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ለዚህም በሕገ መንግስታቸው የሚቀመጠው ድንጋጌ መሰረት ይደረጋል፡ ፡ ነገር ግን መሰል ድንጋጌ በሕገ -መነ ግስታችን ወስጥ ያልተካከተተ በመሆኑ ይህ የአዋጁ አንቀፅ ኢ-ሕገ -መንግስታዊ ይሆናል። በኢፌድሪ ሕገ -መንግስት አንቀፅ 60(2) መሰረት ክልሎችና የፌደራሉ መንግስት የመከባበር ግዴታ ብቻ የተጣለባቸው በመሆኑ የአዋጁ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 6(2) ከሕገ -መንግስቱ ጋር ይጋጫል፡ ፡

3. ከዚህ አዋጅ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት የፍ/ብሔር ሕጉ ለሕጎ ች ግጭት አያያዝ ሕግ አፈፃፀም ወሳኝ አገናኝ ነገር የሆነ ውን መደበኛ ቦታ የሚገዛ እንደመሆኑ አሁን ካለንበት ዘመን ጋር የማይሄዱትን ጉዳዮች ማሻሻል አጠቃሚ ነው፡ ፡ ይህም የሴቶችን መደበኛ ቦታ በተመለከተ የተደነገገውን ይመለከታል፡ ፡ ከኢፌድሪ ሕገ-መንግስት እንዲሁም ተሻሽሎ ከወጣው የቤተሰብ ሕግ አንፃር ያገቡ ሴቶችን መደበኛ ቦታ በተመለከተ የሚወጣው የሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግ ምን አይነት አቆም መውሰድ አለበት የሚለው በአግባቡ መመለስ ይኖርበታል፡ ፡ የ1952ቱ የፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 189(1) እንደሚያስቀምጠው ያገቡ ሴቶች የባላቸውን መደበኛ ቦታ ይወስዳሉ፡ ፡ ያገቡ ሴቶች መደበኛ ቦታ ሊቀይሩ የሚችሉበት ሁኔታዎችን የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ሁለት እንዳስቀመጠው በሁለት ሁኔታዎች ብቻ ይሆናል፡ ፡ በመጀመሪያ ጋብቻው የፈረሰ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ባል በፍርድ ወይም በሕግ የ ተከለከለ ሲሆን እንደሆነ ሕጉ ያስቀምጣል፡ ፡ በመሆኑም የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 35 ያስቀመጠውን የሴቶች እኩልነት መብት ከዚህ አንፃር እንዴት ይታያል የሚለው አስፈላጊ ጥያቄ ይሆናል።

4. እንዲሁም የሕጉን ሥያሜ በመምረጥ ረገድ ተገቢው ትኩት ሊሰጥ ይገባል። በዋናነት አለም አቀፋዊውንም

ሆነ በይነ-ክልላዊ የሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግ ጉዳዮችን የሚገዛ ሕግ ለማውጣት በሚታሰብበት ጊዜ የትኛውን ስም መጠቀም እንደሚያስፈልግ በቅድሚያ መመለስ ያሻል ምክንያቱም በሁሉቱ ስያሜዎች መሃከል ያለው ልዩነት ነው። ስለሆነም ተፈፃሚነት ወይም ተቀባይነት የሌላቸው ውሳኔዎች ሊሰጡ የሚችሉበትን እንዲሁም ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚፃረሩ ሥርዓት በማስወገድ ፍትሃዊና ተገማች የሕግ ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ሕግ ዙሪያ ተቀባይነት ያገኙና ዘመናዊ የሆኑ መርሆችን በመጠቀም በግልፅ የተለያዩ ሁኔታዎችንና ጉዳዮችን የሚደነግግ ሕግና ራሱን የቻለ ሕግ በአጭር ጊዜ ውስጥ መውጣት ይገባል። የሚወጣውም ሕግ ግዛት መረጭ ባልሆነ መልኩ ፍትሃዊና አግባብነት ያለው ውጤት የሚያመጣ በሚሆን መልኩ መቀረፅ አለበት::

5.መሰል ጉዳዮችን ለመግዛት የሚወጣው ሕግ ሕገ-መንግስቱን መሰረት ያደረገና ለተለያዩ የመንግስት አካላት የተሰጡትን ሥልጣንና ግዴታዎች ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል። በተለይ በይነ-ክልላዊ የሕጎች ገጭት አያያዝ ሕግን በተመለከተ የሚወሰዱ እርምጃዎች ሕገ መንግሰታዊ መሆን ይገባቸዋል። በተለይ ይህን ሕግ የማውጣት ሥልጣን የየትኛው አካል ነው የሚለው ጉዳይ በተገቢው ምልኩ በሕገ መንግስቱ ከተቀመጡት የሥልጣን ክፍፍሎችና መርሆች አንፃር ሊታይ ይገባል። በመሆኑም በሕገ -መንግስቱ አንቀፅ 55(6) ላይ የተቀመጠውን ብቻ በመጥቀስ የክልሎችን ይህነሕግ የማውጣት ሥልጣን መጣስ የሚቻል ባለመሆኑ በዚህ በኩል ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡ ፡ ምክንያቱም ይህ አንቀፅ ሊጠቅም የሚችለው የፌደራሉ መንግስት በፌደሬሽን ምክርቤት ውሳኔ አማካኝነት የፌደራል የሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግ እንዲያወጣ ከማድረግ በስተቀር የክልል ሕግ አውጪ አካላት በይነ -ክልላዊ የሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግን ከማውጣት የ ሚያግዳቸው አይሆንም፡ ፡ ስለሆነ ም በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት በአለምአቀፋዊና በይነ -ክልላዊ የ ሕጎች ግጭት አያያዝ ሕግ መሃከል ያለውን ልዩነት ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት።